# የPrairie መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
## የሞባይል ስልክ --- መመሪያዎች እና ስምምነት

ተማሪዎች ቴክኖሎጂን በአስተማማኝ እና በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማስተማር የእለት ተእለት ትምህርት አካል ሆኖ ይቀጥላል። ነገር ግን ሞባይል ስልኮች በክፍል ውስጥ ትኩረትን የሚከፋፍሉ እና የመማሪያ አካባቢን የሚረብሹ መሆናቸው ተረጋግጧል። የተማሪዎቻችንን አካላዊ እና ማህበራዊ ስሜታዊ ጤንነት ለመጠበቅ በንቃት እየሰራን ነው፣ ይህም የሞባይል ስልክ መመሪያዎቻችን እና ስምምነታችን እንደገና እንዲገመገም አድርጓል። ይህ አዲስ ስምምነት የተፈጠረው ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ እና ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት እና የተማሪን ትምህርት ግንባር ቀደም በማድረግ ነው። አሁን ባለው ጥናትና መረጃ መሰረት፣ በትምህርት ጊዜ ልጆች ስልክ አለመያዝ ስልክ የተሻለ ልምምድ እንደሆነ እናውቃለን።

.በተጨማሪም፣ ባለፉት ጥቂት አመታት፣ የተማሪዎችን በትምህርት ቤት የሞባይል ስልክ አጠቃቀም መጨመርን ተመልክተናል። ተማሪዎች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ብቸንነት እና ተፅዕኖ እንደደረሰባቸውም እንረዳለን። የዚህ አንዱ ውጤት በተማሪዎች ላይ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም መጨመር እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህንንም በፕራይሪ(Prairie)፣ በዲስትሪክቱ እና በሀገሪቱ ያሉ ትምህርት ቤቶች እያየን ነው። ለበለጠ መረጃ እባክዎን ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ።

ይህ እንዳለ ሆኖ ፣ ወላጆቻችን/አሳዳጊዎቻችን ተማሪዎች በየቀኑ ስልኮቻቸውን ማግኘት አስፈላጊ እንደሆነ እንደሚሰማቸው እንገነዘባለን። ተማሪዎች ስልኮቻቸውን ወይም ሽቦ አልባ ኦዲዮቻቸውን በካፍቴሪያ ውስጥ ወይም በሜዳ ላይ ለዕረፍት ስወጡ ፣ ከትምህርት ቤት በፊት፣ በምሳ ሰዓታቸው እና ከትምህርት በኋላ ብቻ መጠቀም ይችላሉ።

የፕራይሪ(Prairie) መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት የመግባባት እና የትብብርን አስፈላጊነት ይገነዘባል፣ እና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ኮምፕተሮችን ይሰጣል። በአካዳሚክ ላይ ትኩረት ለማድረግ እና አላስፈላጊ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ለመቀነስ ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን ተግባራዊ ያደርጋል፡-

- ሞባይል ስልኮች እና ሁሉም ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች በሁሉም የመማሪያ ክፍሎች፣ ቤተመጻሕፍት፣ የጋራ ቦታዎች፣ ኮሪደሮች፣ ቢሮዎች ወይም መጸዳጃ ቤቶች ውስጥ መዘጋት ወይም ድምጻቸው መጥፋት አለባቸው።
- ገመድ አልባ የድምጽ መሳሪያዎች በመማሪያ ክፍሎች፣ በቤተመጻሕፍት፣ በጋራ ቦታዎች፣ በኮሪደሮች፣ በቢሮዎች ወይም በመጸዳጃ ቤቶች ውስጥ አይፈቀዱም። (ማለትም፣ ኤርፖድስ፣ ሽቦ አልባ የጆሮ ማዳመጫዎች/ጆሮ ማዳመጫዎች፣ ወዘተ) ተማሪዎች ለትምህርት ዓላማዎች ባለገመድ የጆሮ ማዳመጫዎች/ጆሮ ማዳመጫዎች ሊኖራቸው ይገባል።
- ሞባይል ስልኮች እና የድምጽ መሳሪያዎች ከእይታ ውጭ መሆን እና በተማሪው የግል እቃዎች (ባክባግ፣ ኪስ፣ ቦርሳ፣ ወዘተ) ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።
- ሞባይል ስልኮች እና ሽቦ አልባ የድምጽ መሳሪያዎች በቤት ውስጥ ለቀሩ የኮምፒተር ወይም ባለገመድ የድምጽ መሳሪያዎች ምትክ ሆነው በክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም
- ሞባይል ስልኮች እና የድምጽ መሳሪያዎች በሽግግር ጊዜ ወይም በክፍሎች መካከል ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም
- አንድ ተማሪ በትምህርት ሰአት አስቸኳይ ጥሪ ማድረግ ከፈለገ በክፍል፣ በዋናው ቢሮ እና በክፍል ደረጃ ቢሮዎች ውስጥ የሚገኝ የሕንፃ ስልክ ለመጠቀም መምህራቸውን ሊጠይቅ ይችላል።
- ወላጆች/አሳዳጊዎች አስቸኳይ እና አስፈላጊ መልዕክቶችን ለተማሪዎች ለማስተላለፍ በ 720-747-3200 ወደ ዋናው ቢሮ መደወል ይችላሉ። መልእክቱ ከልጆች ከትምህርት ቤት የመለቀቂያ ሂደቶች ጋር የሚዛመድ ከሆነ፣ ከተቻለ እባኮትን በ2፡30 pm ላይ ይደውሉ

**ተማሪው ስልኩን ይዞ ወይም ሌላ የድምጽ መሳሪያ ሲጠቀም ከተገኘ ቅጣቱ እንደሚከተለው ይሆናል።**

: 1ኛ ጥፋት

- መሳሪያው/ስልኩ በተዘጋ መያዣ ውስጥ በተማሪው ጎን እንዲቀመጥ ይደረጋል እና መምህሩ በሚመችበት ጊዜ ስልኩን በተቆለፈው መያዣ ውስጥ ለዲን ቢሮ ያደርሳል።
- **መሳሪያው/ስልኩ እስከ የትምህርት ቀን መጨረሻ ድረስ በዲን ቢሮ ውስጥ ይጠበቃል**
- ተማሪው በትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ ፈርሞ መሳሪያውን ይወስዳል.
- ወላጆች /አሳዳጊዎች ስልኩ ለዝህ ጉዳይ በተዘጋጀ ማስቀመጫ ዉስጥ መሆኑን ለማሳወቅ ከዲን ቢሮ የኢሜል ወይም የስልክ ጥሪ ይደርሳቸዋል።

**2ተኛ ጥፋት** :

- መሳሪያው በተዘጋ መያዣ ውስጥ ተማሪው አጠገብ እንዲቀመጥ ይደረጋል እና መምህሩ በሚመችበት ጊዜ መሳሪያውን/ስልኩን በተቆለፈው መያዣ ውስጥ ለክፍል ደረጃ ቢሮ ያደርሰዋል።.
- መሳሪያው/ስልኩ በክፍል ደረጃ እስከ የትምህርት ቀን መጨረሻ ድረስ ይቀመጣል።
- **ተማሪው ሪፈር ይደረጋል እና ከቴክኖሎጂ ጋር በተገናኘ የዲስትሪክቱ ቅጣት ተግባራዊ ይሆናል።**
- ተማሪው በትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ ፈርሞ መሳሪያውን/ስልኩን ይወስዳል

- ወላጆች /አሳዳጊዎች  መሳሪያው ስልኩ ለዝህ ጉዳይ በተዘጋጀው  መያዣ ውስጥ መቀመጡን ለማሳወቅ ከክፍል ደረጃ ቢሮ የኢሜል ወይም የስልክ ጥሪ ይደርሳቸዋል።

**3ተኛ ጥፋት**

- መሳሪያው በተዘጋ መያዣ ውስጥ ተማሪው አጠገብ  እንዲቀመጥ ይደረጋል እና መምህሩ በሚመችበት ጊዜ መሳሪያውን/ስልኩን በተቆለፈው መያዣ ውስጥ ለክፍል ደረጃ ቢሮ ያደርሰዋል።.
- መሳሪያው/ስልኩ  በክፍል ደረጃ  እስከ የትምህርት ቀን መጨረሻ ድረስ ይቀመጣል።
- ተማሪው ሪፈራል ይደረግለታል እና የዲስትሪክቱ ቅጣት ከቴክኖሎጂ ጋር በተገናኘ ለሁለተኛ ጥፋት ተግባራዊ ይሆናል።
- ተማሪው በትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ ፈርሞ መሳሪያውን ይወስዳል።

ወላጆች /አሳዳጊዎች  መሳሪያው ስልኩ ለዝህ ጉዳይ በተዘጋጀው  መያዣ ውስጥ መቀመጡን ለማሳወቅ ከክፍል ደረጃ ቢሮ የኢሜል ወይም የስልክ ጥሪ ይደርሳቸዋል።

- **ችግር ለመፍታት ስብሰባ፡  ስልክን በተመለከተ ወደፊት ለመቀጠል  የወላጅ/አሳዳጊ ስብሰባ/የስልክ ኮንፈረንስ ቀጣይ እቅድ ያስፈልጋል።**

**4ተኛ ጥፋት**:

- ***ተማሪዎች  በእያንዳንዱ ቀን መጀመሪያ ላይ ስልካቸውን ወደ ክፍል ደረጃ ቢሮ እንዲያስገቡ  እና በትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ ፈርመው መሳሪያውን/ስልኩን እንዲወስዱ ይጠየቃሉ ።***
- መሳሪያው/ስልኩ  እስከ የትምህርት ቀን መጨረሻ ድረስ በክፍል ደረጃ ቢሮ ውስጥ ይሆናል።

***መሣሪያውን/በተዘጋጀለት መያዣ ዉስጥ  ለማስቀመጥ ፈቃደኛ አለመሆን፡*** ተማሪ እና መሳሪያ/ስልክ  ከሪፈራል ጋር ወደ ዲን ቢሮ ይላካሉ፣ የዲስትሪክቱ ቅጣቶች  ከእምቢተኝነት ጋር በተዛመደ ተግባራዊ ይሆናል።

***ዕቃው ላይ የሚደርስ ጉዳት ;*** ማስቀመጫው  ወይም መቆለፊያው በተማሪው ይዞታ ውስጥ ከተበላሸ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ለመተካት ለሚወጣው ወጪ ተጠያቂ ይሆናሉ።

ግባችን ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ መፍጠር፣ ለመማር ምቹ እና የመማር ሂደቱን ከሚያደናቅፉ መዘናጋት ነጻ ለማድረግ  ነው። ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እነዚህ መመሪያዎች ለምን እንደተወሰዱ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ደስተኞች ነን።.

ትምህርት ቤቱ ለተበላሸ፣ ለጠፋ ወይም ለተሰረቀ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ተጠያቂ አይደለም። ተማሪዎች የግል መሳሪያዎችን ይዘው መምጣት ከመረጡ ደህንነታቸው  የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው።

እባክዎ ያስታውሱ ተማሪዎች በትምህርት ቀን (ከ8፡50 እስከ 3፡45 ፒ.ኤም.) ከምሳ  ሰአት በስተቀር ሞባይል መጠቀም የለባቸውም። **ድንገተኛ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የሚከተሉትን ያድርጉ**

- ለልጅዎ አፋጣኝ መልእክት ማድረስ  ከፈለጉ እባክዎን ወደ ዋናው ቢሮ በ (720) 747-3200 ይደውሉ እና መልእክቱ ለተማሪዎ ይደርሳል
- ከእንግሊዝኛ ውጭ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ቤተሰቦች ወደ ዋናው ቢሮ በ (720) 747-3200 በመደወል የልጅዎን ስም መግለጽ አለባቸው። ቢሮው እርስዎ እንዲያናግሩት ልጅዎን ያገኝልዎታል።

***ይህ መመሪያ በተማሪ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ አለ። ለቀጣይ ድጋፍ እና ትብብርዎ እናመሰግናለን***